**የ2023 የቻይንኛ ተናጋሪዎች ኮንፈረንስ ቁልፍ መግለጫዎች**

*ለጌታ መምጣት ራሳችን ለማዘጋጀት*
*ጌታ ኢየሱስን መውደድ፣ እርሱን እንደ ሕይወታችን መውሰድ፣ እርሱን መኖር፣*
*እርሱን ማጉላት፣ የእርሱን መምጣት መጠባበቅ እና መገለጡን መውደድ ያስፈልገናል፤*
*ይህ የልብ መሻታችን እና ኑሮአችን መሆን አለበት።*

*ለጌታ መምጣት ራሳችንን ለማዘጋጀት*
*ቀኑ እስኪጠባ ድረስ እና ክርስቶስ እንደ ንጋት ኮኮብ*
*በምሥጢር በልባችን ውስጥ እስኪወጣ እና እስኪገለጥ ድረስ*
*በጨለማ ስፍራ ለሚበራ መብራት ጥንቃቄ እንደሚደረግ ለትንቢቱ ቃል መጠንቀቅ አለብን።*

*ለጌታ መምጣት ራሳችንን ለማዘጋጀት*
*ሌሎችን እንመግብ ዘንድ እርሱን እንደ መንፈሳዊ ሙብላችን መደሰት ያስፈልገናል፤*
*የእርሱን ቃል በጸሎት ሁሉ ስንቀበል እና ቃሉን ስናሰላስል እርሱን መደሰት እንችላለን፣*
*ይህም በብዙ ማሰላሰል የእርሱን ቃል መቅመስ እና መደሰት ነው።*

*ለጌታ መምጣት ራሳችንን ለማዘጋጀት*
*ዕለት ዕለት የመታደስ የተነቃቃ ኑሮ መኖር*
*እና በአባታችን እግዚአብሔር የሚያፈቅርና ይቅር ባይ ልብ*
*እና በአዳኛችን ክርስቶስ በእረኝነት የሚንከባከብና የሚፈልግ መንፈስ በእረኝነት መድከም ያስፈልገናል።*

*© 2023 Living Stream Ministry*

**ለዓለም አቀፍ የቻይንኛ ተናጋሪዎች ኮንፈረንስ መልእክቶች**
**የተዘጋጁ አውትላይኖች**
**የካቲት 10-12፣ 2015**

**አጠቃላይ ርዕስ፦**
**ለጌታ መምጣት ራሳችንን ማዘጋጀት**

መልእክት አንድ

**መገለጡን በመውደድ እና የአሁኑን ዘመን ባለመውደድ**
**ለጌታ መምጣት ራሳችንን ማዘጋጀት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 2 ጢሞ. 4፡8፣ 10፣ 18፤ ሮሜ 12፡2፤ 1 ዮሐ. 2፡15፤ 5፡19፤ ራእ. 17፡14፤ 22፡20

**I. የጌታ ሁለተኛ መምጣት ለእኛ ውድ ከሆነ መገኘቱን እንወዳለን—2 ጢሞ. 4፡8፦**

ሀ. የጌታን መገለጥ መውደድ እና ጌታ ራሱን መውደድ ሊነጣጠሉ አይችሉም —1 ቆሮ. 2፡9፤ 2 ጢሞ. 4፡8።

ለ. ጌታ እንዲመጣ የምንጠባበቅ ከሆነ፣ መገለጡን የምንወድ ሰዎች መሆን አለብን —1 ተሰ. 1፡10፤ 2 ጢሞ. 4፡8።

ሐ. የጌታ መገለጥ፣ ተመልሶ መምጣቱ፣ ለእኛ ማስጠንቀቂያ፣ ማበረታቻ እና ማትጊያ ነው—ቁ. 1፣ 18፦

1. የጌታን መገለጥ መውደድ እና መገለጡን በጥብቅ ናፍቆትና በደስታ መጠባበቅ አለብን—ራእ. 22፡20።
2. የጌታን መገለጥ የሚወድ ኑሮ ሊኖረን ይገባል፤ ይህ ደግሞ ተስፋ እንዳንቆርጥ፣ ይልቁንም እስከ መጨረሻ ድረስ ታማኝ ሆነን እንድንቆይ ያደርገናል—2 ጢሞ. 4፡8፤ ራእ. 17፡14።

**II. "ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ…ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም"—1 ዮሐ. 2፡15፦**

ሀ. ዓለም በሰይጣን ብልኃት የተቀናበረ ክፉ ሥርዓት ነው—ቁ. 15-17፤ ያዕ. 4፡4፦

1. ለዓላማው መፈጸም እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ እንዲኖር ፈጠረው፣ ሆኖም ጠላቱ ሰይጣን ሰዎችን በባሕል፣ በትምሕርት፣ በኢንዱስትሪ፣ በንግድ፣ በመዝናኛ እና በኃይማኖት ሥርዓት በማወሳሰብ፣ በእግዚአብሔር የተፈጠረውን ሰው ያለ አግባብ ለመያዝ በምድር ላይ እግዚአብሔርን የሚጻረር የዓለም ሥርዓት ዘረጋ—ኤፌ. 3፡11፤ ዘፍ. 1፡26-28፤ 2፡8-9፤ 4፡16-24።
2. ሰዎችን ለመያዝ እና የእግዚአብሔርን ዓላማ እንዳይፈጽሙ እነርሱን ተስፋ ለማስቆረጥ እና እነርሱን እግዚአብሔርን ከመደሰት ለማስተጓጎል በምድር ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ፣ በተለይ ደግሞ ከሰው ልጆች ጋር የተያያዙት ነገሮች እና በአየሩ ላይ ያሉ ነገሮች፣ በጨለማ መንግሥቱ ውስጥ በሰይጣን ሥርዓት ተቀነባብረዋል—1 ዮሐ. 2፡15-17።
3. ዓለም እግዚአብሔር አባትን ይጻረራል፣ በዓለም ውስጥ ያሉት ነገሮች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይጻረራሉ፣ ዓለምን የሚወዱት ደግሞ የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው—ቁ. 15-17፤ ያዕ. 4፡4።

ለ. "ዓለምም በሞላው፣" ሰይጣናዊው ሥርዓት፣ "በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን"—1 ዮሐ. 5፡19፦

1. "ዓለምም በሞላው" ሰይጣናዊውን የዓለም ሥርዓት እና የዓለምን ሰዎች፣ የወደቀውን የሰው ዘር ያካትታል።
2. "በክፉው እንደተያዘ" ማለት በክፉው አላግባብ መያዝ እና በስልታዊ-ቁጥጥር ክበብ ውስጥ ምላሽ ባለመስጠት መቀመጥ ማለት ነው፤ መላው ዓለም እና የዓለም ሰዎች በሚነጥቀው እና በስልት በሚቆጣጠረው የሰይጣን፣ የክፉው እጅ ምላሽ ባለመስጠት ተቀምጠዋል።
3. በ 1ኛ ዮሐንስ 5፡19 "ክፉው" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል የሚያመለክተው እጅግ የሚጎዳ፣ የሚጎዳ ክፋት ያለው፣ ሌሎችን የሚጎዳ፣ ሰዎች ክፉ እና ጨካኝ እንዲሆኑ ተጽዕኖ የሚያደርገውን ማንነት ነው፤ ዓለምንና ሞላውን የያዘው እንዲህ ያለው ክፉው ሰይጣን፣ ዲያቢሎስ ነው።

ሐ. ሰይጣን ቁሳዊውን ዓለም እና በዓለም ውስጥ ያሉትን ነገሮች በመጨረሻ በክርስቶስ ተቃዋሚው መንግሥት ራስነት ሥር ለመጠቅለል እየተጠቀመባቸው ነው፤ በዚያ ሰዓት የዓለም ሥርዓት የመጨረሻ ጫፍ ላይ ይደርሳል፣ የዚህ ዓለም ሥርዓት እያንዳንዱ ክፍልም የክርስቶስ ተቃዋሚ መሆኑ ይገለጣል—2 ተሰ. 2፡3-12።

**III. የጌታን መገለጥ መውደድ የአሁኑን ዘመን ከመውደድ ጋር ተቃራኒ ነው—2 ጢሞ. 4፡8፣ 10፦**

ሀ. ዘመን የሰይጣን የዓለም ሥርዓት ክፍል ወይም ገጽታ ነው፣ ሰዎችን አታሎ ለመያዝ እና ከእግዚአብሔር እና ከዓላማው እነርሱን ለማራቅ በሰይጣን ጥቅም ሥር ይውላል—1 ዮሐ. 5፡19፤ 2፡15።

ለ. በ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥10 “የአሁኑን ዓለም” የሚያመለክተው የሚከበንን፣ የሚስበንን እና የሚፈትነንን ዘመን ነው፤ ከአሁኑ ዘመን ዓለም ጋር ግንኙነት ከሌለን ከዓለም ጋር ግንኙነት ሊኖረን አይችልም።

ሐ. ዴማስ የአሁኑን ዘመን ወደደ፤ በአሁኑ ዓለም ስለተሳበ ሐዋርያው ጳውሎስን ተወ—ቁ. 10።

መ. በሮሜ 12፥2 ጳውሎስ ይህን ዘመን እንዳንመስል፣ ነገር ግን በአእምሮ መታደስ እንድንለወጥ ይመከረናል፦

1. በቁጥር 2 ይህ ዘመን የሚያመለክተው የአካሉን ሕይወት በመጻረር እና በመተካት የሚቆመውን የአሁኑን፣ ተግባራዊውን፣ የዓለምን ተግባራዊ ክፍል ነው—ቁ. 4-5።
2. ይህን ዘመን መምሰል የዘመኑን ዘመናዊ ፋሽኖችን መከተል ነው፤ መለወጥ ሕይወታዊ ንጥረ-ነገር ወደ ማንነታችን ውስጥ እንዲሠራ መፍቀድ፣ ከዚህም የተነሣ ውስጣዊ ገንባ-አፍራሽ ለውጥ ማምጣት ነው—ቁ. 2፤ 2 ቆሮ. 3፥18።
3. የአሁኑ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን፣ ማለትም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለሚቃወም ልንመስለው አይገባም—ሮሜ 12፥2።
4. በክርስቶስ አካል ውስጥ መኖር ከፈለግን የአሁኑን ዘመን መከተል ወይም ይህን ዘመን መምሰል የለብንም—ቁ. 4-5።

ሠ. የአሁኑን ዘመን ከወደድን ከዓለም ጋር እንወግናለን፤ የጌታን መገኘት ከወደድን ከእርሱ ጋር እንወግናለን፣ ለፍላጎቱም ከእርሱ ጋር አብረን እንዋጋለን —2 ጢሞ. 4፥1-2፣ 4-8፣ 10።

**IV. ጌታን የሚወዱ፣ መምጣቱን የሚጠባበቁ እና መገለጡን የሚወዱ ድል ይነሣሉ—1 ቆሮ. 2፥9፤ 2 ጢሞ. 4፥8፤ ራእ. 22፥20፤ 17፥14፦**

ሀ. የጌታን መገለጥ መውደድ ጌታን እንደምንወድ እና ዛሬ ለእርሱ እንደምንኖር ማረጋገጫ ነው፤ ስለዚህ የእርሱን ሽልማት እንቀበል ዘንድም ቅድመ ሁኔታ ይሆናል—2 ጢሞ. 4፥8፣ 18።

ለ. የጌታን መገለጥ መውደድ ተገቢ ኑሮ መኖር የለብንም ማለት አይደለም፤ ይልቁንም መገለጡን አብልጠን በወደድን መጠን የበለጠ ተገቢ የሆነውን ኑሮ ዛሬ ልንኖር ይገባል—ማቴ. 24፥40-42፤ 2 ተሰ. 1፥10፤ 3፥6-12፤ 1 ጢሞ. 5፥8።

ሐ. ጌታ ኢየሱስን እንደሚወዱ፣ እርሱን እንደ ሕይወታቸው እንደሚወስዱ፣ እርሱን እንደሚኖሩ እና እርሱን እንደሚያጎሉ ሰዎች መምጣቱን የምንጠባበቅ እና መገለጡን የምንወድ መሆን አለብን፤ ወደ ደስታው ለመግባት ተስፋ እንደሚያደርጉ፣ ወደ ጌታ ሰማያዊ መንግሥት እንደሚድኑ እና የጽድቅን አክሊል እንደሚቀበሉ ሰዎች ይህ የልባችን መሻት እና ኑሮአችን መሆን አለበት—2 ጢሞ. 4፥8፣ 18።

*© 2023 Living Stream Ministry*